# *ግለሰባዊ የዲጂታል መዛግብት፤ኢንተርኔትና የመረጃ ደህንነት*

***/ Personal Digital Archive, Internet & Personal Information Privacy/***

***አዘጋጅ፡ አምደሚካኤል አሰማማው***

## *መግቢያ*

ግለሰቦችን አስመልክቶ የሚፈጠሩ ሰነዶች፤አንድም በግለሰቡ በእራሱ የሚፈጥራቸውና የሚያደራጃቸው መረጃዎች ሲሆኑ፤በሀዘን ፣በደስታ እንደዚሁም በተለያዩ ወቅቶች ግለሰቡ በሚያደርጋቸው የእለት ተዕለት እንቅስቃሴ ፤ለማስታወሻነት ጠብቆ የሚይዛቸው የግል መዛግብቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ሰነዶች ለግለሰቡ እንዲሁም ለቅርብ ቤተሰቡና ለሚኖርበት ማህበረሰብ ከታሪካዊና ማህበረሰባዊ ፋይዳቸው አንጻር በጥንቃቄ የሚጠበቁ ግለሰባዊ መዛግብቶች ናቸው፡፡

ግለሰብን አስመልክቶ የሚፈጠሩ መዛግብቶች ግለሰቡ እራሱ አሰባስቦ ከሚይዛቸው የግል ሰነዶች በተጨማሪ መንግስታዊና የንግድ ተቋማት ስለግለሰቡ የሚሰበስቧቸው መረጃዎች ናቸው፡፡እነዚህ መረጃዎች ባዮሜትሪክ እና ዲሞግራፊክ መረጃዎች ሲሆኑ፤ ባዮሜትሪክ መረጃዎች የምንናለቸ ማንኛውም የግለሰቡ ተፈጥሮአዊና አካላዊ መገለጫዎች ሆነው እንደ የእጅ አሻራ፣የአይን አሻራ፣የድምፅ ፣የፊት ምስል እንዲሁም የዲጂታል ፊርማዎችን የሚያጠቃልል ሲሆን ዲሞግራፊክ መረጃዎች የሚባሉት እንደ ሥም፣ዜግነት፣አይማኖት፣የልደት ቀን ፣ጾታ ፣አድራሻ፣ስልክ ወዘተ…ናቸው ፡፡ የግለሰብ መረጃዎች የሚባሉት እንደየ ተቋማቱ የስራ ፀባይ የሚወሰኑ ሲሆኑ የተለያዩ ናቸው፡፡እንደ መገናኛ ብዙሀን ባሉ ተቋማት የግለሰብ መረጃዎች የምንላቸው የጤና፣የትምህርት ፣የሙያዊ፣የግለሰብ ፖለቲካዊ አቋም፣የትዳር ሁኔታ መረጃዎችን እና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ የግለሰብ መረጃዎች በጥንቃቄ ካልተያዙ መረጃዎቹን ያለአግባብ ለመጠቀም በሚፈልጉ አካላት እጅ ስለሚወድቁ የመረጃዎቹ ሚስጥራዊነትና ደህንነት ላይ ተግዳሮትን ይፈጥራል፡፡

የግለሰብ መረጃዎች ላይ ስጋት የሚፈጥሩ ችግሮችን በመለየት ቅድመ ጥንቃቄ ማድግና አጠቃቀማቸውን በተመለከተ ህጋዊ ማህቀፎችን በማዘጋጀት ደህንነታቸውን መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡እነዚህን እጎችን ማወቅ ግለሰባዊ መረጃዎች አጠቃቀምን ፤ሚስጥራዊነትና ደህንነት አጠባበቅን በማስገንዘብ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ እንዲኖር ያደርጋል፡፡በአገራችን የግለሰቦች መረጃ ሚስጥራዊና ደህነትን አስመልክቶ የፀደቁ አዋጆች አሉ፤እነዚህ ህጎችና ደንቦች የዜጎችን መልካም ፈቃደኝነት፣ የተቋማትን ህጋዊ አላማ እንዲሁም የማህበረሰቡን ፍላጎት በዋነኝነት መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡

የዚህ ፅሑፍ ዓላማ ስለግለሰባዊ የዲጂታል መዛግብት ምንነት ግንዛቤን መፍጠር እንዲሁም ግለሰባዊ መረጃዎችን ደህንነት ጥበቃን በተመለከተ ከኢንተርኔት አጠቃቀም ጋር ተያይዞ ያሉትን ተግዳሮቶችና መፍትሔዎችን ለመቃኘት ነው፡፡

## *1. ግለሰባዊ መዛግብቶች*

ግለሰባዊ መዛግብት የመዛግብት ሳይንስ አንዱ ዘርፍ ሲሆን፤ የግለሰቦችን መረጃዎች ጠብቆ የማቆየት ተግባር ነው፡፡ ግለሰቦች ያለፈ ታሪካቸውን የያዙ ሰነዶችን ለቤተሰብ አባላትና ለትውልድ ለማስተላለፍ ጠብቀው የሚያቆዩበት መንገድ ነው፡፡አሁን ባለንበት ዘመን እነዚህ ግለሰባዊ መረጃዎች የሚገኙት በተለያዩ ማህበራዊ ድህረገፆች በመሆናቸው ፤እነዚህን አሰባስቦ ለረዥም ጊዜ ተጠብቀው እንዲቆዩ ማድረግ ነው፡እነዚህ ሰነዶች በፅሑፍ፣በፎቶግራፍ፣በድምፅና ምስል ሊገኙ ይችላሉ፡፡በይዘታቸውም የግለሰቡ ታሪክ የሚያወሱ ሆነው ካላቸው ባህላዊና ታሪካዊ ፋይዳ አንፃር ጠቃሚ ሰነዶች ናቸው፡፡ የግለሰባዊ መዛግብት ባለሙያዎች እነዚህን መዛግብቶች ለማጋራትም ሆነ ይፋዊ በሆኑ ድህረገፆች ላይ ሲያወጡ የግለሰቡን ሕጋዊ መብት በጠበቀና የስነምግባር ደንብን ተከትለው መሆን አለበት፡፡

ግለሰባዊ የዲጂታል መዛግብት አንድ ግለሰብ በኮምፒውተርና መሰል የኤሌክትሮኒክ ቁሶች አማካኝነት አደራጅቶ የሚይዛቸውን መዛግብቶች ናቸው ።ግለሰቦች በመዛግብትነት የሚይዟቸው መረጃዎች በተለያዩ ጊዜያት በሃዘንም ፣በደስታ፣ በዝግጅት ወይም በአጋጣሚ ፣ጠቃሚ የሆኑ እንዲሁም ምንም ረብ የሌላቸው፣ ያልተለመዱ ክስተቶች ወይም ተለምዶአዊ

የእለት ጉዳዮችን የሚዘክሩ መረጃዎች ተከማችተው የሚገኙበት ስብስብ ነው።እነዚህ መረጃዎች በግለሰቡ ኮምፒውተር ፣ ስልክ እንደዚሁም ክላውድ ሰርቨር ላይ ሊገኙ ይችላሉ።

የግለሰባዊ መዛግብት በየዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችን አማካኝነት የምንፈጥራቸው በስልካችንም ሆነ በኮምፒውተሮቻችን ውስጥ የሚገኙ መልዕክቶች፣ድምጾች እንዲሁም ተንቀሳቃሽ ምስሎችን የሚያካትት ነው።እንደዚሁም በማህበራዊ ድዕረ ገጾች ላይ የምናጋራቸው ፎቶግራፎች፣መልዕክቶች ፣ጽሑፎች ሊሆኑ የችላሉ።

የግለሰባዊ የዲጂታል መዛግብት አይማኖታዊ ፣ትምህርታዊ፣ወዳጃዊ፣ በህክምና እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ በሆኑ ጉዶይች ዙሪያ የሚፈጥሩ መረጃዎች፣ የግለሰቡ የዕለት ውሎን የሚገልጹ ጽሑፎች ሆነው በግለሰቡ ቤተሰቦችና እንዲሁም ለሚኖርበት ማህበረሰብ ከታሪካዊ ይዘታቸው አኳያ ጠቃሚ ፋይዳ ያላቸው ናቸው።

በ1980ዓም በመጠናቸው አነስተኛ የሆኑ ኮምፒውተሮች መምጣትን ተከትሎ ግለሰቦች እንደ ፍሎፒ ዲስክ ባሉ ተንቀሳቃሽ የመረጃ ቋቶች አማካኝነት የግል ሰነዶቻቸውን ማደራጀት በመጀመራቸው ምክንያት ግለሰባዊ ዲጂታል መዛግብት እየተለመደ መጣ።የላይብረሪና የመዛግብት ባለሙያዎች ታሪካዊ ይዘት ያላቸውን የግለሰቦችን የዲጂታል መዛግብቶች ማሰባሰብ መጀመራቸው ግለሰባዊ የዲጂታል መዛግብት ይበልጥ እንዲታወቅና እንዲስፋፋ ምክንያት ሆነ። ከ1990ዓ.ም ጀምሮ በአሜሪካና እንግሊዝ የተጀመረው የተለያዩ ድህረ ገጾች የተሰባሰቡበት መዛግብት ለተጠቃሚዎች አገልግሎት ላይ እንዲውል ማድረግ በመጀመሩ ግለሰቦችና የተለያዩ ሀገራት የባህል ማዕከላት አባል የሆኑበት International Internet Preservation Consortium (IIPC) በ2003 ዓ.ም ተቋቋመ።በ2007 እ.አ.አ በአሜሪካን የሚገኘው የኅንግረስ ላይብረሪ የግለሰብ ዲጂታል መዛግብትን አጠቃቀምን በተመለከተ በድዕረ ገጹ ላይ ማስነብብ በመጀመሩ ይበልጥ ግንዛቤን መፍጠር ችሏል።

ለግለሰባዊ የዲጂታል መዛግብቶች የሚደረገው ጥበቃ ከሚቀመጡበት ቋት ፣የመዛግብቱ መጠን እንዲሁም ደህንነቱንና ከምንም አይነት አደጋ የተጠበቀ እንዲሆን የሚደረገውን እንክብካቤ የሚያጠቃልል ነው።

ግለሰቦች የዲጂታል መዛግብቶቻቸውን በሚያደራጁበት ጊዜ ሊዘነጋ የማይገባው እያንዳንዱ መዛግብት በምን አይነት አውድ እንደተፈጠረ የሚገልጽ መረጃ መኖር እንዳለበት ነው።አውዱ በግልጽ የማይታወቅ ከሆነ መረጃው ሊሰጠው የሚችለውን ጠቀሜታ ትርጉም በማሳጣት ይቀንሰዋል።

የግለሰባዊ የዲጂታል መዛግብት ጥበቃ ከሚያጋጥመው ተግዳሮት መካከል፣መዛግብቱ የሚገኝበት የመረጃ ቋት መበላሸት፣በማህበራዊ ድዕረ ገጾች የሚገኙ ፎቶዎች፣ጽሁፎች እና መልዕክቶች መጥፋት፣መዛግብቶቹን የያዘው ኮምፒውተር መበላሸት እንዲሁም ዘመናዊ መተግበሪያዎችና ቁሳቁሶች በሚመጡበት ጊዜ ነባሩ አገልግሎት መስጠት አለመቻል ናቸው።

የግለሰባዊ የዲጂታል መዛግብቶች ፋይዳ መዛግብቱን በሚያደራጀው ግለሰብ ፣ለመዛግብቶቹ በሚሰጠው ዋጋ ልክ የሚያደርግላቸው ተገቢ ጥንቃቅቄና እንክብካቤ እንዲሁም እነዚህ መዛግብቶች በሌሎች አገልግሎት ላይ እንዲውል በመስጥትና በማጋራት የሚወሰን ነው።

## *1.1. ለግለሰባዊ የዲጂታል መዛግብቶች ሊደረግላቸው የሚገባ ጥንቃቄ*

ግላዊ የዲጂታል መዛግብቶች ለረዥም ጊዜ ተጠብቀው አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ፤ ለመረጃዎቹ የምንሰጠው ስያሜ ወጥነት ያለውና መረጃዎቹን በቀላሉ ለመለየት የሚያስችልና አሰናነዳችንም አንድ አይነት ስርዓትን የተከተለ መሆን ይኖርበታል።

መዛግብቶቹ ከመደራጀታቸውና ከተደራጁ በኃላ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ መሰነድ ያለባቸውንና የሌለባቸውን እንዲሁም እንዴት መደራጀት እንደሚገባቸው እቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

እንደዚሁም መረጃዎቹ የሚቀመጡበትን ጥራት ያለው አስተማማኝ የመረጃ ቋት በጥንቃቄ መምረጥ ያስፍልጋል፣ ከዚህ በተጨማሪም ዘመናዊ ቋቶች በሚመጡበት ጊዜ ከነባሩ ወደ ዘመናዊው/Refresh/ማድረግ ያስፈልጋል። መረጃዎቹን

በመጠባበቂያ ቋት/Back Up/ ላይ ማኖር በአጋጣሚ መረጃው ቢጠፋብን እንኳ መልሰን ለማግኘት የሚያስችለን አስተማማኝ ዘዴ ነው።

## 2. የኢንተርኔት አገልግሎትና የግለሰብ መረጃዎች ደህንነት

የመረጃ ሚስጥራዊነት ስንል መረጃዎች ለታቀደላቸው አላማ ብቻ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ ፤ የመረጃዎች አሰባሰብ ፣አጠባበቅ እንዲሁም አጠቃቀም በአንድ አይነት የእግ ማህቀፍና መመሪያ ቁጥጥር ና ጥበቃ ማድገግ ነው፡፡

የመረጃ ደህንነት ስንል መስፈርቶችና ደንቦችን ተግባራዊ በማድረግ ፤መረጃዎች ባልተፈቀደላቸው ተጠቃሚዎች ጥቅም ላይ እንዳይውሉ የማድረግ አንዲሁም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እንዳይቀየሩ፣እንዳይሰረዙና ይፋ እንዳይሆኑ ማድረግ ነው፡፡ይህም በኔትወርክ አማካኝነት የሳይበር ጥቃት እንዳይደርስባቸውና ያለአግባብ እንዳይመዘበሩና ጠቅም ላይ እንዳይውሉ የመጠበቅ ተግባር ነው፡፡

ግለሰብን አስመልክተው ከሚፈጠሩ መረጃዎች አንዱ የመንግስት ተቋማትና እንደዚሁም የዲጂታል ቴክኖሎጂን ተጠቅመው አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት በኢንተርኔት አማካኝነት የሚያሰባስቧቸው የግለሰብ መረጃዎች ናቸው፡፡ እነዚህ መረጃዎች ዜጎች በቴክኖሎጂ የተቀናጀ አገልግሎት እንዲያገኙ፤ የግለሰቦች ሰብሀዊና ሕገመንግስታዊ መብቶች እንዲከበሩ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡እነዚህን መረጃዎች በመጠቀም መረጃዎቹን በመተንነተን እቅዶችንና ፖሊስዎችን ለመቅረፅ እንዲሁም የወደፊቱን በመተንበይ ለአስተዳደራዊ ስራ ጠቃሚ መረጃዎች ናቸው፡፡በእነዚህ ቴክኖሎጂዎች አማካኝነት የሚዘዋወሩ የግለሰብ መረጃዎች ደህንነታቸው ካልተጠበቀ የግለሰቦችን ሚስጥራዊ የመሆን ሙብት ላይ ተግዳሮትን ይፈጥራሉ፡፡

ከእነዚህ ተግዳሮቶች ውስጥ የግለሰቦች ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ የድህረ ገፅ ማስታወቂያዎች/behavioral targeting/ አንዱ ሲሆን ይህም ግለሰቡ በድህረ ገጾች ላይ የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች በመከታተል የግለሰቡን ፍላጎት በማጥናት ፤ ሊፈልገው የሚችለውን ምርቶችና አገልግሎቶች የተመለከቱ ማስታዎቂያዎች ግለሰቡ ወደ ሚጠቀምበት ኮምፒውተር መላክ ነው፡፡ይህን ለማድረግ ግለሰቡ የሚጠቀምበት ኮምፒውተር ላይ *ኩኪስ/Cookies/* እንዲሁም *ዌብ ቤከን/* Web Beacons/ የተባሉ የኮምፒውተር ፕሮግራሞች አማካኝነት ግለሰቡ የሚጎበኛቸውን ድህረገፆች፣ ኢሜሎች እንዲሁም በተለያዩ ማፈላለጊያ ድህረገፆች ላይ በስውር የኮምፒውተሩን መለያ ቁጥር/IP Address/ በመመዝገብ፣የሚሞላውን የማፈላለጊያ ቁልፍ ቃላቶችን በመውሰድ የግለሰቡን አይነተኛ ፍላጎትና ባህሪውን በማጥናት ሊፈልጋቸው የሚችሉ ማስታወቂያዎችን ወደ ግለሰቡ ኮምፒውተር እንዲላክ ያደርጋሉ፡፡አነዚህ የኮምፒውተር ፕሮግራሞች ግለሰቡ የሚጎበኛቸው ድህረ ገጾችን በያዙ ሰርቨሮች አማካኝነት ወደ ግለሰቡ የሚመጡ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ የግለሰቡን ፍቃደኝነት በመጠየቅ ግለሰቡ ሲፈቅድ ከሚጎበኘው ድህረገፅ ላይ ወደ ኮምፒውተሩ የሚገቡ ሲሆን፤ በሌላ ጊዜ ድህረገጹን ሲጎበኝ የሚመጡ ገፆች ከዚህ ቀደም ድህረገጹን ሲጎበኝ በተሰበሰቡት የግለሰቡ ፍላጎቶችና ጥናት መሰረት ማስታወቂያዎችና ተመሳሳይነት ያላቸው ድህረገጾች ወደ ግለሰቡ እንዲመጡ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ዌብ ቤከኖች/Web Beacons/ ግለሰቦች በሚጎበኟቸው ድህረገጾች አማካኝነት ወደ ኮምፒውተሮች የሚገቡ የኮምፒውተር ፕሮግራሞች ሲሆኑ የግለሰቡን እንቅስቃሴ በመከታተል ለምርትና አገልግሎት አቅራቢ ድርጅቶች ስለግለሰቡ የኮምፒውተር አድራሻ ፣ፍላጎትና ዝንባሌ እንዲሁም በኩኪሶዎች አማካኝነት የተሰበሰቡትን መረጃዎች በማቀበል እንደ ግለሰቡ ፍላጎት ማስታወቂዎችና መልህክቶችን እንዲላክ የሚያድርጉ የኮምፒውተር ፕሮግራሞች ናቸው፡፡

የግለሰቦች መረጃ በማስታወቂያ ስራ ላይ በተሰማሩ ድርጅቶች በእጅጉ የሚፈለጉ ጠቃሚ መረጃዎች በመሆናቸው እንደ ጎግል፣ፌስቡክ እና ያሆ በመሳሰሉ ድህረገጾች ብዛት ያላቸው ተጠቃሚዎች የሚሞላቸው ግለሰባዊ መረጃዎች ላይ ጥናት በማድረግና የግለሰቡን ማንነት፣ ፍላጎትና ዝንባሌ በማወቅ ግለሰቡ ሊፈልጋቸው የሚችላቸውን ምርትና አገልግሎቶች ለማስተዋወቅ ይጠቀሙበታል፡፡

የግለሰቦችን ፍላጎት ማህከል ያደረጉ ማስታወቂያዎች/Behavioural Targeting/ ፤የመረጃ ሚስጥራዊነትና ደህንነት ላይ አደጋ ይጥላል ወይስ የምርጫ ጉዳይ ብቻ ነው የሚለው አከራካሪ ቢሆንም በተደረገ ጥናት አብዛኛው ተጠቃሚ ግላዊ ሚስጥሩ እንዲጠበቅ እንደሚፈልግ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ማስታወቂያዎች በራሳቸው ምንም አይነት ችግር

ባይኖራቸውም ስጋቱን የሚፈጥረው ግላዊ ሚስጥርን ማጋለጥ ሊያስከትለው ስለሚችለው ችግር መገመት የማይቻል በመሆኑም ምክንያት ነው፡፡

አንድ የመረጃ ስርዓት/Inforamtion System/ ወደ ትግበራ ሲገባ ለግለሰብም ሆነ ለማህበረሰብ ከሚያመጣው ጠቀሜታ ጎን ለጎን በአጠቃቀሙ ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ ተግዳሮቶቸ ሊኖሩ እንደሚችሉ መገመመት አዳጋች አይሆንም ፤ ለእነዚህ ችግሮች ማህበራዊ እንዲሁም እጋዊ መፍትሄዎችን በማምጣት ቴክኖሎጂው የሚያመጣውን መልካም ነገር በመጠቀም፤ሊፈጠር የሚችለውን ችግሮችም መከላከል ያስፈልጋል፡፡

በኮምፒውተር አማካኝነት የሚሰበሰቡ የግለሰቦች መረጃዎች፤በክሬዲት ካርድ አማካኝነት በሚደረግ ግብይት፣ የስልክ ጥሪዎች፣በምዝገባ የሚከናወኑ አገልግሎቶች፣በባንክና በመንግስታዊ አገልግሎቶች በሚደረግ ምዝገባዎች የሚሰበሰቡ መረጃዎች ፤ ምርትና አገልግሎቶቻቸውን ለትክክለኛ ተጠቃሚዎች ለማድረስ ለሚፈልጉ ድርጅቶች ፤ስለ ግለሰቡ ፍላጎት ፣ ምርጫ፣ ባህሪ፣ ዝንባሌ ፣የኢኮኖሚ አቋም፣እና መሰል መረጃዎች አይነተኛ ምንጮች በመሆን ያገለግላሉ፡፡እነዚህን መረጃዎች የሚያሰባስቡ ተቋማት መረጃውን ለሚፈልጉ መንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ላልሆኑ የንግድ ድርጅቶች ያለ ግለሰቡ ፈቃድ አሳልፈው በሚሰጡበት ወቅት የግለሰቡ መረጃዎች ሚስጥራዊነት ላይ ተግዳሮትን ይፈጥራሉ ፡፡

የግለሰብ ሚስጥራዊ የመሆን መብት/Privacy/ የግለሰቡን ከማንኛውም ክትትል ነፃ የመሆን መብት እንዲሁም መንግስታዊና መንግስታዊ ካሆኑ አካላት ጣልቃ ገብነት ነፃ የመሆን መብት   ነው፡፡የረቀቁ የመረጃ ቴክኖሎጂዎች ይህን የግለሰብ ሚስጥራዊ የመሆን መብት ፤የግለሰቡን መረጃዎች ማግኘት ፣ያለግለሰቡ እውቅና የግለሰቡን እንቅስቃሴ በመከታተል እንዲሁም መረጃዎውችን የማግኛ መንገዱን ቀላልና ትርፋማ በማድረግ በግለሰብ ሚስጥራዊ የመሆን መብት ላይ ከፍተኛ የሚባል ስጋትን ይፈጥራሉ፡፡

የተለያዩ አገራት የግለሰብን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ ህጎችን ተግባራዊ የሚያደርጉ ሲሆን የህጉ ተፈጻሚነት እንደየ አገራቱ የሚለያይ ሲሆን በዋናነት የግለሰቦች መረጃዎች በሶስተኛ አካል ተላልፈው ሲሰጡና ጥቅም ላይ ሲውሉ ግለሰቡ በቅድሚያ ፍቀደኝነቱ ሊጠየቅ እንደሚገባ የሚያስገድዱና ጥቅም ላይ የሚውለው በሌላ አገር ከሆነ ሀገራቶቹ ተመሳሳይ የመረጃ ሚስጥራዊነት አጠባበቅ ህጎችን ተግባራዊ ማድገግ እንዳለባቸው የሚያስገድድ ነው፡፡

## *የመረጃ ቀበኞች*

እስፓይዌር የግለሰቦች የመረጃ ደህንነትና ሚስጥራዊነት ላይ አደጋ የሚፈጥሩ የኮምፒውተር ፕሮግራሞች ሲሆኑ ፤ በተለያዩ መተግበሪያ ሶፍትዌሮች ውስጥ እራሳቸውን በመደበቅ ግለሱቡ መተግበሪያውን በሚጠቀምበት ጊዜ እያንዳንዱን የግለሰቡን እንቅስቃሴ በማጥናት መረጃዎችን ለሶስተኛ ወገን የሚያቀብል የኮምፒውተር ፕሮግራሞች ናቸው፡፡

በኢንተርኔት ከሚከናወኑ የስራ እንቅስቃሴዎች ጋር ተያይዞ ማለትም እንደ ባንክና ኢንሹራንስ ያሉ ገንዘብ ነክ አገልግሎቶችን በሚጠቀሙ ግለሰቦች ላይ የሚያጋጥመው የኢንተርኔት የወንጀል ተግባር አንዱ ፊሺንግ ነው፤ ግለሰቡ ከሚጠቀምበት ድህረ ገፅ የመጣ አስቸኳይ መልዕክት እንዳለ ተጠቃሚውን በማሳመን ሚስጥራዊ የመለያ ቁጥሩንና ሚስጥራዊ ቁልፉን ተጠቅሞ ወደ ተሳሳተና ተመሳስሎ ወደ ተሰራው ድህረገፅ ላይ የግል መረጃዎቹን እንዲያስገባ በማድረግ መረጃዎቹን ለወንጀል ተግባር መጠቀም ሲሆን ለዚህም እንደመፍትሄ የሚሆነውና ተጠቃሚዎች  ከተላከላቸው መልዕክት ላይ በሚገኝ ማስፈንሪያ/ሊንክ/ አገልግሎት ወደሚያገኙበት የድርጅት ድህረገፅ ከመሄድ ይልቅ፤ ትክክለኛ የድህረ ገጹን አድራሻ በማስገባት በቀጥታ ወደ ድህረገጹ መሄድ ለእንደዚህ አይነቱ ችግር ከመጋለጥ ይታደጋል፡፡

በኢንተርኔት አገልግሎትና የኤሌክትሮኒክ ንግድ አማካኝነት የግለሰቦችን መረጃ ያለአግባብ በመጠቀም  ከሚፈፀሙ ወንጀሎች አንዱ የማንነት ስርቆት የሚባለው የኢንተርኔት የማጭበርበር ወንጀል ፤በድብቅ የተገኘውን የግለሰቦች መረጃ እንደ የመታወቂያ ቁጥር፣የመንጃ ፈቃድ መለያና የክሬዲት ካርድ ቁጥርን በመጠቀም አገልግሎቱን ለእራሳቸው ማግኘት እንዲሁም በእገወጥ መንገድ  ሌሎች አገልግሎቶችን መጠቀም ሲሆን ለዚህ የኤሌክትሮኒክ ንግድ ድህረገፆች  የግለሰቦችን ስም፣አድራሻና ፣ስልክ ቁጥር የሚያገኙበት መንገድ ነው፡፡

## *ማጠቃለያ*

ግለሰቦች የሚፈጥሯቸውን የግል መዛግብቶች በጥንቃቄ መሰነድና የተፈጠሩበትን አውድ የሚገልጹ መረጃዎችን ከመዛግብቱ ጋር መሰነድ ይኖርበታል፤እነዚህ መረጃዎች ዲጂታል ከሆኑ የመዛግብቶቹን ቅጂ ደህንነቱ የተጠበቀ ስፍራ ላይ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

የግል መረጃዎችን የሚጠይቁ ደህረ ገፆች ላይ የሚሞሉ የግለሰብ መረጃዎች ድህረገጹ ከደንበኞቹ ጋር ግለሰባዊ መረጃዎችን በተመለከተ ተግባራዊ የሚያደርጋቸውን ህጎችና ደንቦች መብቶችና ግዴታዎችን የሚገልፀውን የአገልግሎት ውል ተገንዝቦ መሆን ይኖርበታል፡፡ኢንተርኔትን በምንጠቀምበት ወቅት ወደ ኮምፒውተሮቻችን የሚመጡትን ኩኪሶችና ዌብ ቤከኖችን የመረጃዎቻችንን ሚስጥራዊነት ባገናዘበ መልኩ እንዳይጫኑ መወሰን ያስፈልጋል፡፡

ኮምፒውተሮቻችን ላይ አንቲቫይረሶችንና አንቲ እስፓይዌሮችን በመጫን ከመተግበሪያዎች ጋር ወደ ኮምፒውተሮቻችን የሚገቡ ማልዌሮችን መከላከል ይቻላል፡፡በአገራችንና እንደዚሁም በአለምአቀፍ ደረጃ ተግባራዊ የሚሆኑ የመረጃ አጠቃቀም ህጎችንና ደንቦችን በማወቅና ተግባራዊ በማድረግ ፤ግለሰባዊ መረጃዎችን ሚስጥራዊነትና ደህንነትን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

## *ምንጮች*


- *Managing information system, Kenneth C.Laudon & Jane P.Laudon*
- *Basic computer course book, Free University of Bolzano Bozen – Dr. Paolo Coletti - Edition 8.0 (25 January 2015)*
- *Ethiopia - Data Protection Overview ,October 2023*
- *https://en.wikipedia.org/wiki/Information_privacy_law*
- *https://en.wikipedia.org/wiki/Personal_archiving*
- *https://www.ohchr.org/en/privacy-in-the-digital-age*
- *https://arapahoelibraries.org/blogs/post/personal-archiving-what-is-it/*